# የሰነደ፡ ሙዓለ፡ ንዋይ፡ ገበያ፡ አይነቶች

# Major Types of Securities Market

## የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ




## ሁለተኛ ደረጃ ገበያ




PRAGMA INVESTMENT ADVISORY
Your Vision, Our Process

swipe

# የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ
## PRIMARY MARKET

በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፩፪፻፵፰/፳፻፲፫ ዓ.ም አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፵፱ መሰረት የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ማለት በውክልና ሻጮች አስተባባሪነት አዳዲስ አክሲዮኖችን፣ ቦንዶችን፣ የተሰፋ ሰነድችን፣ እና ሌሎች ገንዘባዊ ሰነዶችን በመሸጥ አዲስ ካፒታል የሚሰበሰብባቸው ገበያ ናቸው።

According to the Ethiopian Capital Market Proclamation **№1248 /2021** in article 2 sub article 49 the definition of Primary Market is a market facilitated by underwriters in which new capital is created or raised by selling newly issued stocks, bonds, notes, and other financial instruments.



የመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ማለት ለመጀመሪያ ጊዜ አዳዲስ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለግብይት የሚቀርቡበት እና ድርጅቶች፣ መንግስት እና ሌሎች ተቋማት ጥሬ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሰነደ ሙዓለንዋዮቻቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለህዝብ የሚሸጡበት የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ነው። ይህ ገበያ የመጀመሪያ ደረጃ የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ በመባል ይታወቃል።

The primary market is a financial market where new securities are issued and sold by companies, governments, and other groups to obtain financing. It is where securities are created and sold for the first time to the public. The primary market is also known as the new issue market.



# ለምሳሌ

## For Example

አንድ አርሶ አደር ያመረተውን ምርት ባካባቢው ለሚገኝ አንድ ነጋዴ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሽያጭ በማቅረብ ምርቱን እንደሚሸጥ ሁሉ እንደዚሁ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ለሕዝብ ሽያጪ ሲቀርቡ እንደ መጀመሪያ ደረጃ  ገበያ ይቆጠራል።

When a farmer sells their product to a local trader for the first time, it's considered the primary market. Similarly, in the securities market, when securities are offered for sale to the public for the first time, it's considered the primary market.

# ሁለተኛ ደረጃ ገበያ

## SECONDARY MARKET

በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፲፪፻፵፰/፳፻፲፫ ዓ.ም አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፷፩ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማለት ኢንቬስተሮች በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ በቀጥታ ከአውጪው ወይም ከአገናኙ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሚገዙበት ውጪ አስቀድመው የወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ከሌሎች ኢንቬስተሮች የሚገዙበት ገበያ ማለት ነው።

According to the Ethiopian Capital Market Proclamation **№1248 /2021** in article 2 sub article 61 the definition of Secondary Market is a market where investors buy previously issued securities from other investors instead of issuer or an intermediary.



ሁለተኛ ደረጃ ገበያ ማለት ደግሞ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ውስጥ ካለፉ በኋላ እንደገና ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በድጋሚ የሚሸጡበት ገበያ ነው። ባለሀብቶች በተቀላጠፈ መልኩ ከሌሎች ባለሀብቶች ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እንዲገዙ እና እንዲሸጡ ያስችላቸዋል።

The secondary market is where securities are traded after they go through the primary market. It provides liquidity and allows investors to buy and sell securities from other investors.



ሁለት ዋና ዋና የሁለተኛ ደረጃ ገበያ አይነቶች አሉ እነሱም የተማከለ የሰነደሙዓለንዋዮች ገበያ እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎች ናቸው።

There are two primary types of secondary markets: Securities exchanges and over-the-counter markets.

# ለምሳሌ

## For Example

በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ምርቱን በቀጥታ ከአርሶ አደሩ የገዛው ነጋዴ ለሌላ ነጋዴ በተሻለ ዋጋ የገዛውን ምርት ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚሸጠው ሁሉ በተመሳሳይ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ ገበያ ላይ ቀድመው ተሸጠው የነበሩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በድጋሜ ለሁለተኛ ጊዜ ለሽያጪ ሲቀርቡ እና ሲሸጡ እንደ ሁለተኛ ደረጃ ገበያ የቆጠራል።

In the primary market, when a trader buys a product directly from a farmer and then sells it to another trader at a higher price. Similarly, in the securities market, when securities that were previously sold in the primary market are offered for sale again, it is considered the secondary market.

Like & Share If You Found This Post Helpful.

PRAGMA
INVESTMENT ADVISORY
Your Vision, Our Process